# ትላንትን አንርሳ! ቆሞ ቀር የዛሬ አዝማሪዎችም አንሁን!

ሠይፈ ደርቤ

ቻይናውያን የስልጣኔያቸውን ምንጭና መነሻ አይረሱም፤ በዚያው ስልጣኔም ላይ ቆመው አያዘምሩም። ስለትላንት በማውራትና በማወደስ የበቀቀን ያህል ችኮ አይሆኑም። ጥሩና መጥፎውን ይለያሉ፤ ለእያንዳንዱም ዋጋ ሰጥተው ካለፈው ተሞክሯቸው ይማራሉ፤ ስህተታቸውን ያስተካክላሉ፤ እድገታቸውን የሚያፋጥኑ የነገ ሰዎች ይሆናሉ። ብዙ ትላንቶችን ወደ ዛሬ፣ ብዙ ዛሬዎችንም ወደ ነገ ቀይረው አሳይተውናል። እኛስ እንዴት ነን?...

የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አባላትም ይሁኑ የቻይና መንግስት ለህዝባቸው ጥሩና ፍትሃዊ ነገር ከመስራት ባሻገር በስህተታቸውም ራሳቸውን ተችተው ነገ የተሻለ ስራ ለመስራት ቀዳሚ ትኩረት ይሰጣሉ። ማህበረሰባቸውም በዚያው አንፃር የተቃኘ በመሆኑ ጥሩና መጥፎውን በምክንያት ይለያል፤ ለጥሩውም ለመጥፎውም ዋጋ ይሰጣል።

በዚያው ሚዛን መሪውን መንግስትና ፓርቲ ይዳኛል። የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ የኮሚንታንግ አመራርን ሲያስወግድ ቀዳሚው ተዋናይ ህዝቡ ነበር። ህዝቡ በኮሚንታንግ አመራር የሙስና ተግባርና በስርዓቱ ውስጥ በነበረው ስር የሰደደ ንቅዘት እንዲሁም የፊውዳሎች ጭቆና ያለ ቅጥ ተማርሯል።

በዚሁ ወቅት ኮሙኒስት ፓርቲው የህዝቡን ጥያቄ ይዞ ተነሳ፣ ህዝቡም ደገፈው፤ ህዝቡ ግን በአንድ ጊዜ አልደገፈውም። እንዲያውም ብዙው ህዝብ መጀመሪያ ተጠራጥሮታል። በሂደት ግን የኮምኒስት ፓርቲው ዓላማ እየገባው ሄደ።

ፓርቲው የኮሚንታንግን ፓርቲ ሲያባርር ብዙዎቹ ተቋማት ከኮሚንታንግ ጋር አብረው ተሰድደው ነበር። ካዝናውም ባዶ ከመሆን ብዙ ያልራቀ ነበር። በባዶ የተነሳው የቻይና መንግስት ዛሬ እዚህ ደረጃ ላይ እንዴት ደረሰ ብለን እናስብ።...

ከኮሚንታንግ መሸሽ በኋላም የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ ከፖለቲካ ስራው ጎን ለጎን በታላላቅ የልማት ጉዳዮች ተጠመደ። የወቅቱ የቻይና መሪ ማኦ ዜዱንግ የአዲሲቷ ቻይና መመስረትን እንደ

አውሮፓውያን አቆጣጠር በ 1949 ይፋ ካደረጉ በኋላ የሶስት ዓመት ጉዞአችውን የተስፈነጠረ ለማድረግ Great Leap Forward በማለት ታላቅ አብዮት አወጁ።

ወቅቱን ታሳቢ ባላደረገው ታላቅ የልማት ጉጉታቸው ሌላ አብዮት በቀጣይ መድገማቸውም እውን ሊሆን ዋዜማ ሆነ። በዚያን ወቅት ግን ሁለተኛው እቅዳቸው አልታወቀም ነበር። ያም ሆኖ ሁለቱም ለውጥ ናፋቂ እቅዶቻቸው ከባድ ኪሳራና ውድቀት እንዲሁም የህዝብ ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው። በዚያው ውስጥ ብዙ ስራዎች መሰራታቸው ባይካድም።

እነዚህኑ ስህተቶች ኮሙኒስት ፓርቲው ኃላፊነት ወስዶባቸው፣ ሊያስተካክላቸውና ከስህተቶቹም ሊማርባቸው ቃል ገብቶ ስራውን ቀጠለ። ፓርቲው ለችግሮቹ መከሰት ራሱን ባለቤት አድርጎ ስህተቱን ለማስተካከል ከመስራት በስቲያ ተፈጥሯዊ አደጋና ሌላ ምክንያትን በሰበብነት በመደርደር አልተጓዘም። ህዝቡም ይህንኑ ያውቅ ነበርና ለኮሙኒስት ፓርቲው ድጋፉን ባለመንፈግ ሌላ እድል ሰጠው።

ፓርቲው በዚያው እድል በመጠቀም ልማቱንም አጠናክሮ በመቀጠል ህዝብ ሊያማርሩ እና እምነት ሊያሳጡ የሚችሉ ንቅዘቶች እንዳይፈፀሙ አምርሮ በመታገል ስራውን አጠናከረ፤ የስታሊን አስተምህሮ ስር በሰደደበት ሶቪየት ህብረት ቀኖናውን ይዘው ሲጓዙ የነበሩት ሶቪየታውያን ሲፈራርሱ፣ ለስርዓቱም መወደቅ የተለያዩ ምክንያቶችን ሲሰጡ፣ ቻይና ግን በራሷ ሞዴል ሶሻሊስታዊ ስርዓቷን ይዛ ዘለቀች።

ይህም የቻይና ሶሻሊስታዊ ስርዓት ከሶቪየት የተቀዳ እንዳልሆነ፣ ከንክኪውም የበለጠ መራቅ እንዳለበት ያስገነዘበ መሆኑን ዜዱንግ የሚመሩት ኮሙኒስት ፓርቲ ተገንዝቦ ቻይና በራሷ ሞዴል ሶሻሊስታዊ የገበያ ኢኮኖሚዋን ይበልጥ አጠናክራ እንደምትቀጥል ተናገሩ። ህዝቡና መንግስቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደጉ የቻይና ኢኮኖሚ 1 ነጥብ 3 ቢሊየን የዓለማችንን ህዝቦች ቀልቦ ማኖር ቻለ።

ቻይናውያን ማኦ ዜዱንግን የአዲሲቷ ቻይና መስራች አባት ይሏቸዋል፤ ዴንግ ዢያኦፒንግን ደግሞ ሪፎርሚስት ወይም የለውጥ አባት በማለት ያሞካሿቸዋል።

እነዚህ ሁለት ታላላቅ መሪዎች ለቻይና ኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን ለቻይና ዓለም አቀፍ

ኃያልነት ተጎናፅፎ ታላቅ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ገናኖች ናቸው። በሀገሪቱ የምጡቅ አስተሳሰብ ባለቤትም ተደርገው መታየት ከጀመሩ ቆይቷል።

የአዲሲቷ ቻይና መስራች አባት ተደርገው የሚታዩትና በኮሙኒስት ፓርቲውም ሆነ በቻይና ህዝብ ዓርማ ሆነው የዘለቁት ዜዱንግ በመሪነት ዘመናቸው የፈፀማቸው ሁለት ታላላቅ ስህተቶች እንደ መስራች አባት ከመወደስ፣ ዋጋ ከማግኘትና በታላቅነታቸው ከመዝለቅ አላገዷቸውም።

ዜዱንግ በ 1952 ቻይናን ለታላቅ ኪሳራ ህዝቡን ደግሞ ለከፍተኛ ረሃብ ዳረጉበት በሚባለው የ Great Leap Forward ንቅናቄና እሱኑ ተከትሎ ከሶስት ዓመታት በኋላ Cultural Revolution ብለው በተነሱለት ለ 10 ዓመት የዘለቀ መርሃቸው ያደረሱትን ጥፋት በተለይ ምዕራባውያን አሁን ድረስ በማብጠልጠል፣ ሌሎች ተሳስተዋል የሚሏቸውን ቅጥያዎችም በመጨመር የሰውየውን ማንነት ሌላ ገፅታ ቢሰጡትም፣ ኸዮፒንግ ግን «አሁንም ቢሆን ዜዱንግ የአዲሲቷ ቻይና መስራች አባት መሆናቸው ሊታወቅ ይገባል» ይላሉ።

እሳቸው በቀረጿቸውና ሊተገብሯቸው በሞከሯቸው ሁለት «ታላላቅ ስህተቶች» ውስጥ ብዙ መሰረተ ልማቶች፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ተገኝተዋል የሚሉት ኀዮፒንግ ስህተቱ መርሃቸው ሳይሆን መርሁ የተፈፀመበት ወቅት ጊዜውን የጠበቀ አለመሆኑ ነው ይላሉ። አሁን ቻይና ለደረሰችበት ሁሉን አቀፍ ስኬት የዜዱንግ አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑንም ይገልፃሉ። የዜዱንግን ሀገራዊ አስተሳሰብ እና ራዕይ ለማሳካት አሁንም ቻይና እየሰራች መሆኑን ይጠቁማሉ።

ቻይናውያን ሁልጊዜም ቢሆን ስህተታቸውን እንደ መምህራቸው ይቆጥሩታል። ስህተት ወዲያውኑ መታረም እስከቻለ ድረስ መጥፎ ተደርጎ መወሰድ የለበትም ይላሉ። ስህተት ነገ ሌላ መጥፎ ድርጊት እንዳይደገም ትምህርትና ልምድ የሚቀሰምበት፣ የተሻለ ርዕይ የሚወለድበት አስተማሪ ተግባር መሆኑንም ያምናሉ። ስህተት ለለውጥ መነሻ መሆኑንም ይገልፃሉ።

በትላንቱ አስተምህሮና ድርጊት ላይ ተመስርቶ መዝለቅ ጥሩ ቢሆንም ማሻሻያዎችን እየጨመሩ መጓዝ ካልተቻለ አንድ ስርዓት ለመዝለቁ አስተማማኝ አመክንዮ ማግኘት ከባድ መሆኑንም ይጠቁማሉ። የሶቪየትን መፈራረስ በስታሊን አስተምህሮ ቁዘማ ውስጥ እውን የሆነ ነው በሚል

የሚተቹት ቻይናውያን፣ የማኦ ዜዱንግን አስተምህሮና ርዕይ ስንፈፅመው በርዕዩ ላይ በመመስረት፣ ማሻሻያዎችንም በማድረግ፣ ከትላንት ስህተትም በመማር ነው ይላሉ።

በእያንዳንዱ ጉዞ ያለ «ንቁ መሪ» ሰው በመሆኑ ይሳሳታል፤ ከስህተቱ ይልቅ ጥሩው ጎኑ ስለሚያመዝን ጥሩውን እያጠናከሩ፣ መጥፎውን እያረሙ መጓዝ የግድ ይላል በማለት ይመሰክራሉ። በአንድ ስርዓት ጉዞ መሪው ለነበረው እድገት ወይም ውድቀት ቀዳሚውና የመጀመሪያው ቢሆንም እድገቱም ሆነ ውድቀቱ በአንድ ሰው የመጣና የተፈፀመ ተደርጎ መታየት እንደሌለበትም ጠንከር አድርገው ይናገራሉ።

ማኦ ዜዱንግ በዘመናቸው የሰሯቸው ስራዎች ዘመን አይሽሬ ናቸው የሚሉት ዢዮፒንግ፣ በተፈፀሙ ስህተቶችም ውስጥ ኮሙኒስት ፓርቲውና መንግስታቸው የለበትም ማለት አይደለም፤ ከተፈፀመው ስህተት ይልቅ የተሰራው ስራና የቻይና የብልፅግና ጉዞ ግዘፍ የነሳ፣ በህዝብም የተመረጠና የቀጠለ ነው ይላሉ።

ነገር ግን ዜዱንግ በህይወት እያሉም ጭምር ስህተቶቻውን ነቅሰው በማውጣት ስህተቱ ለምን እንደተፈፀመም ሳይንሳዊ ማብራሪያ ጭምር በመስጠት ኃላፊነት ወስደዋል። እንደ ዜዱንግ ያሉ መሪዎች እድለኞች የሚሆኑት ከዚህም አኳያ ነው። ዜዱንግ ብቻ ሳይሆኑ የቻይና ህዝብም አንዱ የእድሉ ባለቤት ነው ማለት የሚያስችለው የስህተቱ ምንጭና መነሻ ምን እንደሆነ ተገንዝቦ በሚዛናዊነት መቆሙም ጭምር ነው።

ዜዱንግ ባወጡት መርህ ከ 20 ሚሊየን የሚልቁ የቻይና ገጠር ነዋሪዎች ወደ ከተማ መጥተው ታላቅ በተባሉ ስራዎች እንዲሰማሩ ከተደረገ በኋላ በደረሰው ኪሳራ ስራዎቻቸውን ጥለው ወደ መጡበት ገጠር እንዲመለሱ ሲደረግ ሁኔታውን ያለ ምንም ማቅማማት አሜን ብለው ተቀብለዋል። የተዘጉ ተቋማትና በህዝቡ ላይ የደረሰው መከራም ምንጩ የተፈጥሮ አደጋ ነው በሚል ማታለያ አልተሸፈነም።

ኢኮኖሚው ምንም በሌለው የቻይና መንግስት እንዲያ አጓጉል ሲጓዝ፣ የውጭ ባለሃብቶችም ሆኑ ሌሎች እንዲሳተፉበት እድል በሌለበት ታላቁ ሩጫ መክኖ ሲቀር ዜዱንግ ፊት ለፊት ቆመው

ህዝባቸውን ይቅርታ ከመጠየቅ ሌላ አልተሸሸጉም፤ መላ ነው ያሉትን ሌላ ሃሳብና እቅድም ይዘው ከመምጣት አልቦዘኑም፣ ተስፋም አልቆረጡም።

ማኦ በዚህ ብቻ ሳይሆን ፓርቲያቸው ውስጥ ባላቸውም አቋም የተወደሱ ናቸው። አሁን ከ80 ሚሊየን የሚልቀው የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አባል በእሳቸው ጊዜም ቀላል ቁጥር አልነበረውም። ከምንም በላይ መንግስታቸውና ፓርቲያቸው የህዝብ አመኔታን እንዲያተርፍ ራሳቸውን ሞዴል አድርገው አቅርበዋል። ሙስናን ፈፅሞ የማይደራደሩት፣ እኛ ኪራይ ሰብሳቢነት የምንለውን የመስገብገብ ዝንባሌ አምረረው የሚጠሉ የቻይና የቁርጥ ቀን ልጅም ናቸው።

እሳቸው አዲሲቷን ቻይና ከመሰረቱ በኋላ ለረጅም ዓመታት የደመወዝ ጭማሪ የናፈቀው ሰራተኛው በኢኮኖሚው መነቃቃት ጭማሪ ሲያገኝ፣ ራሳቸውን አርአያ በማድረግ ህይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ በኑሮ ውድነቱ ጊዜ እንዲቀነስባቸው ያደረጉትን ደመወዝ ይዘው በመቀጠል፣ ከከፍተኛ ባለስልጣናቱ ይልቅ ታችኛው ሰራተኛና አመራር የተሻለ ተከፋይ እንዲሆን የማድረግ ስልት ተከትለዋል።

በዚህ ፅሁፍ ኢህአዴግና የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ በባህሪ የሚመሳሰሉባቸውን ሁኔታዎች በጥቂቱ እንይ፣ አመራሩ ሊማራቸው የሚገቡ ጉዳዮችንም እንመለከት።

ኢህአዴግ እንደ Great Leap Forward አይነት ስህተት ተሳስቷል ማለት ባይቻልም፣ ዓለማዊ ሁኔታውም ለዚህ አይነቱ ስህተት እድል ባይሰጠውም፣ ጠንቃቃ ባይሆኖ ኖሮ ከዚህ ስህተት የሚያግደው እንደሌለ በፅኑ መግለፅ ያግባባል።

ከጨለማ ወደ ብርሃን በሚደረገው ጉዞ ኢትዮጵያ ያካሄደችው ታላቅ የልማት አብዮት ከአምስት ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ጋር የተያያዘ ነው። ቻይና ስራ የነበራቸው የህዝቧ 1/13ኛ የሚሆኑ 20 ሚሊየን ዜጎቿ ስራ አጥ ሆነው ወደመጡበት ገጠር ሲመለሱ፣ ኢትዮጵያ ለ3 ሚሊየን ዜጎች የስራ እድል መፍጠሯን በእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱ 4ኛ ዓመት አረጋግጣለች።

ቻይና በታላቁ እንቅስቃሴዋ መዳከም ሳቢያ ተቋማቶቿ ሲዘጉ፣ ህዝቧም ለከፋ ረሃብ እና ችግር

ሲዳረግ ኢትዮጵያ በዓለማችን ካሉ አስር ፈጣን ኢኮኖሚ እየተመዘገበባቸው ካሉ ሀገራት አንዱ መሆኗ ተረጋግጧል። የዜጎቿ የነፍስ ወከፍ ገቢም በዚያው ልክ ማደጉ ተገልጿል።

ቻይና በአስርና 13 የሚገመቱ የስዊዝ ካናል አይነት ግድቦችን በፍጥነት በመገደብ ህዝቧን በየጊዜው አየበላው ካለው የጎርፍ አደጋ ስትከላከልና ውሃዋን ለልማት ስታውል ኢትዮጵያም ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በመላው ህዝቧ ርብርብ ከመገንባት ጉዞ ባሻገር በርካታ አረንጓዴ ኢኮኖሚን ታሳቢ ያደረጉ የሃይል ልማት ግንባታ ስራዎችን እያከናወነች ነው። ውድድሩን በማብዛትና የሩጫ መጠኑን በማርዘም ጥግ ድረስ መሄድ ይቻላል።

የኢኮኖሚ ሩጫውን ጉዳይ ትተን ወደ ዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጉዞ እናምራ። ቻይና፣ ዢዮፒንግም እንደሚያረጋግጡት ልማት በፍጥነት ርምጃ የሚያስፈልገው፣ ዴሞክራሲ ግን በሂደት የሚሳካ በመሆኑ ቀስ በቀስ ልንጓዝበት የሚገባው ነው ስትል፣ ኢትዮጵያ ልማትና ዴሞክራሲ አይለያዩም፣ ይኸው የህልውና ጉዳይ ነው በማለት ሁለቱንም አብሮ የማስኬድ አጀንዳዋን አጠናክራ ቀጥላለች።

ትምህርት ትምህርት ነውና ሌላም ትምህርት እንውሰድ። ኢትዮጵያ በታላቁ መሪያችን የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ፈር ቀዳጅና ግምባር ቀደም አስተዋፅኦ አሁን ለደረሰችበት ደረጃ መብቃቷን ማንም ህሊና ያለው ሊክደው አይችልም። አሳቸው በነበሩበት ዘመን ግን ምንም ስህተት አልነበረም ብሎ መናገር አይቻልም። እሳቸውም በህይወት ሳሉ በትግል ዘመን ጭምር ኢህአዴግ ከራሱ ስህተት አየተማረ ራሱን ያሻሻለ ፓርቲ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግስትም ካለፈው ስህተቱ በመማር አዳዲስ አስተሳሰቦችን በመከተልና በማራመድ ወደፊት እየገሰገሰ ውጤትም እያስገኘ መሆኑን ገልፀዋል። ኢህአዴግ ከተማረባቸው ጉዳዮች አንዱ ከምርጫ 97 ጋር ይያያዛል። በወቅቱ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ የነበረውን ምርጫ ተከትሎ ጥቂቶች ባስነሱት ህገወጥነት በርካታ ሰዎች ሞተዋል።

ለብጥብጡም ሆነ ለአመፅ ፈጣሪዎቹ ምቹ ሁኔታ የፈጠረው ምንድን ነው የሚለው ሲታይ ብዙ ማለት ቢቻልም፣ በዋናነት የምርጫ ሰነ ምግባር ህግና ደንብ አለመኖሩ ነው በዬ በግሌ

እከራከራለሁ። ይህን ችግር አሁን በተግባር ላይ ያለው የምርጫ ሰነ ምግባር ህግና የፓርቲዎች ደንብ ይፈተዋል፣ ፈትቶታልም ብዬ አምናለሁ። ምርጫው በሰላማዊ ውድድር መድረክ እንዲካሄድ እድል የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን የሚያስገድድም የስነ ምግባር ደንብ አለመውጣቱ ህዝቡን እንመራለን የሚሉ ፓርቲዎች ሽንፈታቸውን በፀጋ ባለመቀበል፣ ውጤቱም በገለልተኛው ምርጫ ቦርድ በኩል እስኪገለፅ ባለመጠበቅ የፈጠሩት ወከባ ለብዙዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። እናም መንግስትን የሚመራው ኢህአዴግ ካለፈው ስህተቱ በመማር እንደ መንግስት የፓርቲዎች የስነ ምግባር ደንብ እንዲወጣና ራሱ ኢህአዴግን ጨምሮ በሁሉም ወገኖች እንዲከበር አድርጓል። ይህን ትምህርት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

አሁንም ኢህአዴግ እና መንግስት ሊማሯቸው የሚገቡ ጉዳዮች ግን አሉ። ከኢህአዴግም ሌሎች መማር ያለባቸው ጉዳዮች ይኖራሉ። ህጋዊነትንና ልማታዊነትንና ለዴሞክራሲ ጉዳይ ትኩረት መሰጠትን ሌሎች ከኢህአዴግ ሊማሩ ይገባል።

ኢህአዴግም በመለስ አስተምህሮና ራዕይ ላይ የተመሰረተ Elastic Reform በየዘርፎቹ መማርና መንቀሳቀስ ይኖርበታል። ፖሊሲ በየጊዜው ተለዋዋጭ መሆን አይኖርበትም። ልማት ቀጣይ እና የሚያድግ መሆን አለበት። የፖሊሲ መለዋወጥ ህዝብን ግራ ማጋባትና ርዕይን ማጣት ነው። ነገር ግን መለስ በህይወት ቢኖሩ ኖሮ ምን ያህሎቹን ጉዳዮች ከስንት ጊዜ በኋላ ሊመለከቷቸው ይችላሉ ብሎ መጠየቅ አለበት። ተወደደም ተጠላ መለስ የዘመን ክስተት ነው። ዘመን የፈጠረው፣ ዘመንም መልሶ የማይፈጥረው፣ ነገር ግን እሱን የተረዳው ሃይል መለስ የሰራው ላይ ተመስርቶ ሪፎርሙን እንደሚያፋጥን የማይታበል ሀቅ ነው።

ምናልባት ዛሬ ላይ የምንለውጠው፣ ወይም የምንቀይረው ላይኖረን ይችላል። ዛሬ ላይ ሆነን ግን መለስ የሰራውን ብቻ በመፈፀም መታጠር አይኖርብንም። ታላቁ መሪያችን ይዞአቸው የተነሳቸውን መስመሮች ጠብቀን፣ አዳዲስ ቀመሮችም አበጅተን በፍጥነት የምንሮጥ፣ ዛሬ ያሰብነውን ነገ ልንቀይር የምንችል የለውጥ ሃይል መሆን ይገባናል።

ሌላው ልንማርበት የሚገባው ጉዳይ ሙስናን አምርሮ የመታገልና እያንዳንዱ ኃላፊ ሞዴል ሆኖ

የመውጣት ጉዳይ ነው። መለስ በሙስና ላይ የነበረው አቋም ይታወቃል ብቻ ሳይሆን ሀገራችን ኢትዮጵያም እሱ በቀደደው የፀረ ሙስና መስመር፣ ያለመዝቀጥ እና ኪረቃይ ያለመሰብሰብ አሰተምህሮ በሙስና ብዙ አትታማም የተባለበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። ነገር ግን ጠቅላይ የቀድሞው ሚኒስትራችን አቶ መለስ ይሉት እንደነበረው በዚህ ወጤት መዘናጋት አይኖርብንም። ዝንባሌያችን በኪራይ መሰብሰብ ላይ ከታጠረም ህዝብ ይሸሸናል፤ ልናስተባብረውና ልንመራውም ያስቸግረናል። ስለዚህም የሙስና ደረጃ የለውም ብለን ጥግ ደረስ መታገል ይኖርብናል።

ቆሞ ቀር ጥፋት ፈላጊና ጥፋት ነቃሾች ብቻም ሳንሆን የልማት ዘዋሪዎች ሪፎርሚስቶች መሆንም ይገባናል። በየዘርፉ ያለ አመራር እቅድ ሲጎድልበት፣ ጥፋት ሲሰራ ምክንያት እየደረደረ ህዝብ የሚያውቀውን ሳይክድ በግልፅ ችግሩን የሚናገር፣ ይቅርታም የሚጠይቅ፣ ከስህተቱም የሚማርና በፍጥነት የሚያርም ሊሆን ይገባል። ይህም ሌላው ትምህርት ሆኖ ሊወሰድ ይገባል። ሌላውን ሌላ ጊዜ የምንማርበት እንዲሆን በቀጣይ ብቅ የምል ሆኖ ለዛሬው በዚህ አበቃሁ።